xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን
xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx

ዲሞ ቅጽ 12 ቁ 3 ሰኔ/1978

# "ሕገ—መንግስቱ"

ፋሽስታዊው መንግስት የጭቆና፣ የምዝበራ፣ የጠበርና የጨፍጨፋ አገዛዙን ለመሸፋፈን ያልተከናነበው ሻሽ፣ ያላጠለቀው ቆብ፣ ያላንቀረቀረው ዘፈን የለም:: መልሶ መላልሶ በዚሁ ከመቀጠል ሌላ የሚሆንለት ባለመሆኑም በአርከስ ተግባሩ የተጋለጠ ውስጠ—ባህሪውን ለመጋረድ አሁንም ባዲስ መልክ ሲታከት ይገኛል::

የጠቀቱ መሯሯጥ ደግሞ "ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" የሚሉትን ማዐዱ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ፕሬዚዳንትነትን ማረጋገጥ ሆኗል:: ለዚሁ የሚውልና የሚያገለግል "የሕገ—መንግስት ረቂቅ" የፋሽስቱ ጥርቅም አዘጋጅቶ እራሱ ጋባዥ እራሱ ተጋባዥ የሆነበት ከመሆኑም በላይ ሕዝቡ በግድ የበዴ—ተመልካችነቱን በአለልታ እንዲያስተጋባ [illegible] ተመዝሎ፣ ሰይፉም ተንቀሳቅሷል::

"ኢትዮጵያ ትቅደም" ብሎ ጭፍጨፋው ያው፣ "በኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ሲሞለመ" ብሎ ምዝበራና ምንተፋው ያው፣ ተመለሰውም "በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሽየታ ካሄደ ነው" ብሎ ርዝፍና አርዛቱ ያው ሆኖ እያለ መንግስቱ ኃ/ማርያም እንኳንስ እራሱን ፕሬዚዳንት ብሎ መሰየም ይቅርና ከጠመው አጼ፣ ንጉሠ—ነገሥት ነኝ ብሎ ዘውዱ ቢጭን ከሕዝቡ ጥቅም፣ መብት፣ ሰላምና እድገት አንፃር የቀንጣት ያህል መሻሻልን የሚያስከትል አይሆንም::

ኢትዮጵያ ሀብታም የሆነችበት ጥቂት ነገሮች ቢኖሯ አንዱ የአዋጅ ጋጋታ ነው:: ይህም አለበቃ ብሎ ገን በቅርቡ ኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሆናለች": ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስትም ተጐናፅፋለች ወዘተ ብሎ ሊታወጅ ሽር ጉድ ጠፏል::

ከሕገ—መንግስቱ አወጣ አንፃር ምናልባት አዲስ ወይም ለውጥ ያለው ነገር ቢኖር "ለውይይት የቀረበ ረቂቅ" መባሉና ፋሽስቶች የተወሰኑ ትርዒቶች በውይይት ስም ካካሄዱ በኋላ "የሕዝቡ ተካትፍ ውጤት ነው" ብለው ጥቃቅን የቃላትና የአስካክ ቅያሬዎች በረቂቁ ላይ ቷደርገው ባነጋሪቱ ጋዜጣ ሊታወጁ መታቀዱ ነው:: ለውጥ አለ ቢባል መንግስቱ ኃ/ማርያም፣ ፍፀም ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን መሆኑን እንደቀደምቶቹ አዋጆች /ኢስፓክን የመሠረቱት አዋጅ ለምሳሌ/ በግልህ ከማስቀመጥ ይልቅ "ፕሬዚዳንቱ በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣል" ወዘተ በሚሉ አቀራረቦች ሽፋፍኖ ያንኑ ስልጣን እንደጨበጠ ለማስቀጠል ያደረጉት የማደናገሪያ ጥረቶች፣ ባይሳካላቸውም፣ ላቅ ያለ መሆኑ ነው:: ለውጥ አለ ቢባል የፋሽስቱ ጥርቅም የቢለሟሎቹንና የፍርፋሪ ለቃሚያቹን ቁጥር ሰፋና ጨመር አርጉ ሊያስኬዱ የሚችሉ፣ በአንፃሩም በሕዝብ ላይ ጭቆናና ምዝበራውን ሰላላ መንገዱ ለማራመድ የሚያመች መንግስታዊ መዋቅሮቹን በይበልጥ ከማስፋፋትና ከማጠናከር አንፃር ጎላ ያለ ትኩረት የተሰጠበት መሆኑ ነው::

ይመሰረታል የሚሉት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከቶም ሕዝባዊ ሆነ ዲሞክራሲያዊ ሊሆን እንደማይችል በተለያዩ ሁኔታዎችና ወቅቶች ተደጋግሞ የተገለፀ ነው:: ለዚሁ ሕ.ዲ.ሪ.ኢ. ለሚሉትም መሠረት ይሆናል ብለው የሚዘጋጁትም "ሕገ—መንግሥት" በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ከሀቀኛው ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሕገ—መንግሥት ጋር ያለው ዝምድና ግፋ ቢል የከሰል አመድ ከስንዴ ዱቄት ጋር ካለው መመሳሰል በላይ የሚሄድ አይደለም::

ይህ ሕገ—መንግስት የሚሉት ነገር የተነደፈው ሀቀኛ የሕዝቡ ወኪሎች ባልተካፈሉበት፣ የፖለቲካ ስልጣኑ ሙሉ በሙሉ በፋሽስቶች ጥርቅም መዳፍ ውስጥ በሆነበት ወዘተ ሁኔታዎች መሆኑ ለማንም የእውነት ጠባና ላልሆነ ሁሉ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ጉዳይ ነው:: የ"ሕገ—መንግስቱን ረቂቅ" ያዘጋጀው ስብስብ የፋሽስቱ ጥርቅም አባላት በአብዛኛው የተካፈሉበት፣ ለዚሁ ጥርቅም ያደሩ "ምሁራን" በተሰጣቸው ቀጥር የታከሉበት፣ በኢሠፓ ሙሉ ቁጥጥር ስር ካሉ ማህበሮች ወኪል የተካሉ —ለጥርቅሙ ታማኝ አገልጋይ የሆኑ— ግለሰቦች የተጨመሩበት ሌሎች ምንም ዓይነት ሚና ሊኖራቸው የማይችሉ ጥቂት ግለሰቦች [ለምሳሌ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ ሃጂ መሐመድ ሳኒ፣ ቄስ ፍራንሲስ እስቲፋኖስ፣ ጥላሁን ገሠሠ ወዘተ] ለይስሙላ ጠብ—ጠብ የተደረጉበት፣ ባጠቃላይ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ሙሉ ቁጥጥር ስር የሆነና በሱ የተሾሙ አባላትን ያጠቃለለ ስብስብ ነው:: ይህ የመንግ ስቱ ኃ/ማርያም ፍጡር ነው እንግዲህ "የሕገ—መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን" ብሎ የካቲት 7/77 ላይ በነጋሪት ጋዜጣ ታውጆ በመንግስቱ ኃ/ማርያም ሊቀመንበርነት፣ በፍቅረ ስላሴ ወግደረስ ም/ሊቀመንበርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክሎ የሕገ—መንግስት ረቂቅ አዘጋጀ የሚባለው::

በቀርጡም ይኸው ጉዳ ተለዕኮየን አገባደዱት ብሎ [በግልፅ የመንግስቱ ኃ/ማርያምን ፈላጭ ቆራጭ ንጉሠ—ነገሥትነት ከማስቀመጥ በመለስ] ሊቀመንበሩን ማንገሻ ሰነድ አቀርቧል:: ይህንንም የሕገ—መንግስት ረቂቅ ብሎ በሰማያዊ ፊደላትና በቀይ ሮዕስ አሽበርቆ፣ በመጀመሪያው ገጽ የላይኛው ጠርዝ ላይ "ሠርቶአደሩ ሕዝብ ---- በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ቀጥተኛ ንቁና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማድረጉ አጅግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የትግሉ ውጤቶች ዋናውና መብቱ ነው:: ---ጓድ መንግሥቱ ኃ/ማ፣ ነሐሴ 1977 ---" የሚለውን በቀይ ቀለም የተፃፈ መግቢያ ጥቅስ አክሎ በሚሊዮን ኮፒዎች በትኗል:: በዚሁም መሠረት ዲሞክራሲያዊ ውይይት በህዝቡ እየተካሄደ ነው ብሎ ለማሳመን ይኸው የፋሽስቶች ጥርቅም ኢሠፓን፣ የመንግስት መዋቅራን፣ ኤምባሲዎችን፣ የውጭ አገር ደጋፊዎችን ወዘተ አንቀሳቅሷል::

ፋሽስቶች የሚሉትን ይበሉ እንጂ የፖለቲካ ስልጣን ሙሉ በሙሉ በመዳፋቸው ውስጥ ሆኖ፣ ዲሞክራሲ ደብዛውና ሽታው በጠፋበት ሁኔታ የሚታወጀው ሕገ—መንግሥት ከደርግ፣ ከኢሠፓአኮ፣ ከኢሠፓ ሕገ—ማህበር ሰነዶች ሆነ አዋጆች አወጣጥና አቀራረብ ልዩነት ካለው የቀርፅ እንጂ የይዘት አለመሆኑን ለመገንዘብ ጠቢብነት የሚጠይቅ አይደለም:: ሕገ—መንግስቱ "ረቂቅ"፣ "ለውይይት የቀረበ" ተባለ አልተባለ፣ በመንግስቱ ኃ/ማርያም የሬዝ ጥቅስ ተኳረከ አልተኳረከ ቲፎታፊዎቹ አነሱ፣ ወሬኞቹ አነሱ፣ ተጠያሚዎቹ እነሱ መሆናቸውን ለመካድ ከቶም የሚቻላቸው አይሆንም:: ረቂቅነቱ የአብረተኛ ፊዝነቱ ብቻ ነው:: "ለውይይት የቀረበ" የሚለውም ርቱዕ አየታየ እንዳለው የኢሠፓ ባለስልጣ ናቸውንና ካድሬዎችን "ማብራሪያዎች" [ለዛውም መሠረታዊ ነጥቦች ላይ ሳያተኩሩ] ለአንድ ሁለት ቀናት ያህል የመስማትና ውይይቱ አብቃ ሲባልም በረቂቅ ላይ የሰፈረውን፣ "እና የኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ፣ ሙሉ የስልጣን ባለቤትነታችን የሚገልፀበትን፣ ---- ሕ.ዲ.ሪ.ኢ.ን የሚመሠረትበትንና የሚተዳደርበትን የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን ይህን ሕገ መንግስት ከ__________ እስከ __________19__ ባደረግነው ውሳኔ

ሕዝብ አጸድቀናል“[ሕገ–መንግስት ረቂቅ፣ መቅደም] የሚለውን፣ አሜን/ ምስጋና ለመንግስቱ ኃ/ማርያም ይግባው/ ብሎ ለማፅደቅ የመዘጋጀት ግዴታን ነው::

ጠለቅ አድርጎ በዝርዝር ላጤነው ይቅርና ላይ ላዩን ወይም ገረፍ ገረፍ አድርጎ ለተመለከተው እንኳን ከዚህም ከዚያም ተሳጥፎና ተኳኩሎ የቀረበው “የሕገ–መንግስት ረቂቅ” ገና ሲነካኩት ለጥፉ ሲለቀ፣ቀርፊቱ ሲረገፍ ይታያል::

የመንግስት ስልጣን ብፋሽስቶቹ ጥርቅም መዳፍ ተጠቃሎ የሚቀጥል መሆኑን ለመሸፈፈን “በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያ ሪፑብሊክ ስልጣን የሠርቶአደሩ ሕዝብ ነው” ተብሏል [ሕገ–መንግስት ረቂቅ፣ አንቀጽ 3 ቁ1፣ገጽ 2]:: ሠርቶአደሩ ሕዝብ ማለት የፋሽስቶቹን ጥርቅም ለማለት ካልተከጀለ በስተቀር ይህ ቅጥፈት እንኳንስ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያውቅን ይቅርና “ኢትዮጵያ” የሚለውን ቃል አንድ ሁለቴ የሰማ ባይታዋርን እንኳን ለማታለል መቻሉ የሚያጠራጥር ነው:: እንዲያው ቢጋጣሚ በዚህ አመርቃኝ አረፍተ ነገር ግር የሚሰኝ አንባቢ ቢገኝ ግር ታው ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ አይቆይ አይኖረውም:: “የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የአገሪቷ የእድገት አቅጣጫ ቀያሽ፣ የመንግስትና የመላ ኅብረተሰብ መሪ ኃይል ነው”[አንቀጽ 6 ቁ2፣ ገጽ2] የሚለው አረፍተ ነገር የረቂቁ ተመልካች ለሆነው ሰው እንኳን ቢያንስ ስልጣን በተባለው ፓርቲ እጅ መጠራቀሙን ይጠቁምለታል:: ጉዳዩን በቅርብና በተጠያቂነት ለሚያውቀው ደግሞ በሚባለው ሪፑብሊክ ስልጣን ሙሉ በሙሉ በፋሽስቶቹ ፓርቲ፣ በኢሠፓ፣ በተለይም በፈላጭ ቆራጩ መንግሥቱ ኃ/ማርያም እጅ እንደሚሆን ለገዳፍታም የሚስተው አይሆንም::

በርግጥ አሁንም አካሉን ቶቶ በጥላው ላተከረ፣“የብሔራዊ ሸንጎ” ስልጣንና ተግባር ተብለው ለይስሙላ ከተዘረዘሩት መሐል ብሔራዊው ሸንጎ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፕሬዚዳንትን ... ይመርጣል በመባሉ [አ.64. ቁ4] ፕሬዚዳንቱ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚመረጥ ለመስለው ይችላል:: ይህ ግን ከቶ ሊሆን የሚችል፣ በታም የሚኖረው ጉዳይ አይደለም:: ኢሠፓ “ቀያሽና መሪ ኃይል ነው” ከሚለው ጋር ተያይዞ “ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ዕጩዎች በኢሠፓ አካላት፣ በሕዝባዊ ድርጅቶች፣ በወታደራዊ ክፍሎችና በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣቸው አካላት ይጠቆማሉ”[አ.65] የተባለው ለዋዛ አይደለም:: የሸንጎው አባላት የሚመረጡበት ሆነ ሌላውንም የሚመርጡበት ሁኔታ በዚህም በዚያም ተብሎ በኢሠፓ ቁጥጥር ስር እንደሚሆን በፅሁፍ ደረጃ ከሰፈረው ብቻ እንኳን መገመት አዳጋች አይሆንም:: የኢሠፓአከ፣ ለጥቆም የኢሠፓ፣ ከዚያም የመኢሠማ፣ መኢገማ፣ ወዘተ “ሸንጎዎች” አነማንን እንዴት ለምርጫ እንደሚጠቁሙና እንደሚመርጡ፣ የሸንጎዎቹ አባላት ሚና ውሱንነት ምን ያህል እንደሆነ ወዘተ በአለፉት ዓመታት ገሀድ የወጡ ጉዳዮች በመሆናቸው አሁን በሕገ–መንግስቱ ረቂቅ መሠረት ሊቋቋም የታቀደውም “የሪፑብሊኩ ብሔራዊ ሸንጎ” ከነዚሁ በይዘት የተለየ ሕልውና ወይም ሊጨወት የሚችለው ሚና ይኖረዋል ብሎ መገመት ቢያንስ የፖለቲካ የዋህነት ይሆናል::

እዚህ ላይ መንግስቱ ኃ/ማርያም ራሱን የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ አድርጎ ሲሰይም፣ [እነሱ ሲመረጥ ይሉታል] በጥቀማው ወቅተበብ ቸኛ ተወዳዳሪነት የተዘከረለትን ውዳሴ–መንግሥቱ እንደገና ማስታወሱ ጠቃሚ ይሆናል:-

> “ብልህነት፣ ቆራጥነት፣ የሕዝብ ወገንነትና ትዕግሥት ከአርቆ አስተዋይነት ጋር የተዋሃደበት፣ አመራር በመስጠት የታሪክ ሂደት ውስጥ ራሱን ያስከሰተ፣ ከሁሉ ልቆ የታየና ---- የዋና ፀሐፊነትን ተግባር በተሟላ ሁኔታ ሊያከናውን የሚችል”፣ “ታላቅ የፖለቲካ ሰው”፣ “በራስ አነሳሽነት የቀየሳቸው የአመራር ጥበቦች ዓለምን ያስደነቁ”፣“ወሳኝ መሪ”፣“የታላቅ አብዮት ምርጥ ፍሬና የኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ አኩሪ የትግል ውጤት”፣ “ተደናቂ ወታደራዊ ጥበብ ያሳዩ ብቁ የጦር አዝማች”፣ “ደግና ደግና የጦር መኮንን”“ወደር–የለሽ አርቆ አስተዋይ፣ በሀቅ የተወደደ፣ የተከበረ፣ ብቃቱ በተግባር የተረጋገጠ”፣ “ወደር–የሌለው ዕውነተኛና ሃቀኛ መሪ” --- ነው /ናቸው ተብሏል::

መንግስቱ ኃ/ማርያም ለፕሬዚዳንትነት ለ"ብሔራዊ ሸንጎው" በሚጠቆምበትም ጊዜ እላይ የተጠቀሰው ለጆሮ የሚቀፍ ውዳሴ ከዚያን ወዲህ ወደ ሰሜን ኮርያ ከተደረጉ ምልልሶች በተገኘ ተጨማሪ ተመክሮ ዳብሮ፣ ይበልጥ እንገሸጋሸ ሆኖ ይቀርብ እንደሆን እንጂ በምርጫው አካሄድና ውጤት ላይ ጉልህ ለውጥ መጠበቅ ለምኞቱ ይቅር ለሕልም አያመችም።

ለነገሩ፣ መንግስቱ ኃ/ማርያም፣ በሕግ ተደነገገ አልተደነገገ፣ ፕሬዚዳንት ብቻ አይደለም የሚሆነው ፈላጭ ቆራጭ ፕሬዚዳንት እንጂ። ይህም ሆኖ በሕገ-መንግስቱ ረቂቅ ላይ የፕሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባርን አስመልክቶ የሰፈረውም ቢሆን ይህንኑ በበቂ ያበሰራል። ፕሬዚዳንቱ "ርዕሰ-መንግስት ነው"፣ "ሪፐብሊኩን በውስጥና በውጭ ይወክላል"፣ "የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው" [አ.86. ቁ1-3]። ፕሬዚዳንቱ "የአገሪቷን የውስጥና የውጭ ፖለሲ በተግባር መተርጎሙን ያረጋግጣል"፣ "ጠቅላይ ሚኒስትርን ... የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን፣ ም/ፕሬዚዳንትንና ዳኞችን፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን፣ የብሔራዊ ሠርቶአደር ቁጥጥር ኮሚቴ ሊ/መንበርን፣ ዋና ኦዲተርን ለብሔራዊ ሸንጎ አቅርቦ ያስመርጣል"፣ የተመረጡት መ/ቤቶች "የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣታቸውን ያረጋግጣል" [አ.87. ቁ1 ሀ-መ]። ፕሬዚዳንቱ "ዓለምአቀፍ ውሎችን ይዋዋላል" [አ.87. ቁ2-ሀ]፣ የመከላከያ ምክር ቤት አባላትን ይሾማል፣ ምክር ቤቱን ይሰበስባል" [አ.87. ቁ3] ወዘተ፣ወዘተ።

እንግዲህ ለይስሙላም ቢሆን በአንድ ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል የተባለው "ብሔራዊ ሸንጎ" ሙሉ ስልጣኑን [ስልጣን አለው ከተባለ] ለማን አስረክቦ እንደሚገኝ ግልፅ ነው። የፕሬዚዳንቱ ሥልጣን እላይ የተጠቀሱት ብቻም አይደሉ። ፕሬዚዳንቱ አመቺና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሯል በሚል ሳቢያ ያሻውን ሊያደርግ የሚያስችለው ተጨማሪ ሥልጣን ሰፊ ገብቷል። በዚህ መሠረት ለምሳሌ ፕሬዚዳንቱ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሯል ብሎ የወቅቱን ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ም/ጠቅላይ ሚኒስትሮችንና የምክር ቤቱን አባላት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትሎቹን፣ ዳኞችን፣ ጠቅላይ አቃቤ ሕግን፣ ወዘተ እንዳሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሽሮ በምትካቸው አዲሶችን ሊሾም ይችላል [አ.88. ቁ1-ሀ]። ይህን ማድረጉ በሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጎ ስብሰባ ቀርቦ መፅደቅ እንዳለበት መጠቀሱ [አ. 88. ቁ1-ለ] በፕሬዚዳንቱ ልዩ ሥልጣንና ይህንንም ተግባራዊ አድርጉ በሚኖረው ውጤት ላይ እምብዛም ለውጥ ያስከትላል ተብሎ የሚጠበቅ አይደለም። በተጨማሪ ፕሬዚዳንቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ለማዋል ሕግ ማውጣት ካስፈለገው "የፕሬዚዳንት ድንጋጌዎችን" ሊያወጣ ስለሚችል [አ.87. ቁ1-4] በዚህም አማካኝነት ሥልጣኑ ወሰን አለው ከተባለ ድንበሩን ለማስፋፋት መሣሪያው ተቀብሎ በእጁ ያለ በመሆኑ የለመደው ሌባ ጣቱ ምላጩን በየጊዜው ከመሳብ የሚቦዝን አይሆንም። ባጭሩ እንግዲህ መንግስቱ ኃ/ማርያም በየአምስት ዓመቱ የዘውድ በዓሉን የሚያከብር፣ ለስሙ ፕሬዚዳንት በተጨባጭ ግን ፈላጭ ቆራጭ አጼ የሚሆንበትን ክስተት ነው 'ኢ.ህ.ዲ.ሪ.ን'፣ የኢ.ህ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ወዘተ በሚሉ ማደናገሪያዎች ሕዝቡ ይምታለናል ተብሎ ልብ-ውልቅ ውልቅልቅ እየተባለ ያለው።

መቸም የፋሽስቶቹ ሕገ-መንግስት በአንዳንድ ነገሮች ከሌሎች በጣም የላቀ ነው። በሕዝብ ላይ አምባገነኖች ያላቸውን ንቀትና የሚያሳዩትን እብሪት ከማንፀባረቅ አንፃር የሚያስንቁት ካሉ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። እንኳንስ የንግግር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ፣ ወዘተ መብት ሊኖር እነሱ የሚፈልጉትን አለመናገር፣ አለመፃፍ፣ በመፈክርና በሰልፍ አለማስተጋባት ወዘተ በሚያስቀጣበት ሀገር የሕዝቡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሕገ-መንግስቱ ይረጋገጣል ይሉናል።ለስሚው ትዕግስቱን ይስጠውና:- "የኢትዮጵያውያን የንግግር፣ የፅሁፍ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ትዕይንተ ሕዝብ የማድረግና በማህበር የመደራጀት

ኑፏኗኝ-ያተረጋገጠ ነው [አ.48. ቁ1]፤ የኢትዮጵያውያን ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር ነፃነት የተረጋገጠ ነው [አ.49. ቁ 1]፤ የኢትዮጵያውያን የመልዕክት ምስጢርነት የተረጋገጠ ነው [አ.50. ቁ.1) የኢትዮጵያውያን ሰብአና አለመደፈር የተረጋገጠ ነው [አ.44 ቁ1]፤ የኢትዮጵያውያን መኖሪያ ቤት አለመደፈር የተረጋገጠ ነው [አ44. ቁ2]፤ የኢትዮጵያውያን የኅሊናና የሃይማኖት ነፃነት የተረጋገጠ ነው [አ.47. ቁ1]፤ ወዘተ፣ወዘተ:: ምንም እንኳን የሕዝቡ በፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀት፣ የሠራተኞች የስራ ማቆም አድማ የማድረግ፣ የብሔር/ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን ወዘተ መብቶች የተሰረዙና አንዳንድ መብቶችም "ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር" ወዘተ በሚሉ ሐረጎች የተገደቡ ቢሆኑም፣በሕገ መንግስቱ ረቂቅ የኢትዮጵያውያን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ምልተው እስከሚፈሱ ተረጋግጠዋል።እንግዲህ ምን ቀረ/ ምን ጐደለ/

በዚህ ላይ ብዙ ማለት የሚያሻ አያሿንም:: በጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት፣ በኢሠፓአኮና በኢሠፓ አገዛዝ ስር እነዚህ ሁሉ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ተረጋግጠውለታል እየተባለ መፈክሮች የተስተጋቡበት፣ ግጥሞች፣ መዝሙሮችና ዘፈኖች ሳይቀሩ የተዘጋጁበት ወዘተ መሆኑ ግልፅ ነው:: በሶቭየት ዩኒየንም ሆነ በሌሎች ዴሞክራሲ ደብዛው በጠፋባቸው ወይም እየጠፋ ባለባቸው ሃገሮች እነዚህና ተመሳሳይ መብቶች በሕገ—መንግስት ደረጃ ተረጋግጠዋል እየተባሉ ያሉበት መሆኑ የሚካድ አይደለም:: ችግሩ በሕገ—መንግስት ወዘተ ደረጃ በፅሁፍ የሰፈሩትና በተግባር የሚውሉት ወይም በተጨባጭ ገነው የሚታዩት ሁኔታዎች እንደ ሰማይና ምድር ተራርቀው የሚገኙ መሆናቸው ላይ ነው:: በዚህ ረገድ በፋሽስቶቹ የሕገ-መንግስት ረቂቅ ላይ የቀረ ወይም የጐደለ ነገር ቢኖር ከሁለት አንዱን ማረግ ነው:: ወይ "ኢትዮጵያውያን ማለት መንግስቱ ኃ/ማርያምና ጭፍሮቹን ብቻ ማለት ነው" የሚለውን ትርጉም እና እነዚህ ግለሰቦች "የሰፊውን ሕዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመርገጥ መብታቸው የተረጋገጠ ነው" የሚለውን ማከል [ይህን ማድረግ የፌዝቸውን ደረቅነት ሊያጠነዝው ይችል ይሆናል ግን ከአብሪተኛነት አንፃር ለሚያስቀጥረው ተጨማሪ ነቀብ ሊካካስ ስለሚችል ከግምት ሊያስገቡት የሚገባቸው አይሆንም] አለዚያም ቀለል ሌል የሚችለውን ሌላ አማራጭ መውሰድ፣— "የተረጋገጠ ነው"በማለት ፈንታ ፊደል—"ጋ"ን ሰርዞ "የተረገጠ ነው" ማለት ወይም ደግሞ "የተረገጠ፣ የተረጋጋጠ ነው"ብሎ ግልፅነት መስጠት።እንግዲህ በዚህ አኳያ የቀረ ነገር ቢኖር ከነዚህ አማራጮች አንዱን ደፈር ብሎ ወስዶ ወደ ሀቁ ጠጋ ማለት ነው::

ሌሎችም (የሕገ—መንግስቱ ረቂቅ) ከነሳቸውም ሆነ ሳይጠቅስ ወይም በማስተሳለፍ ከዘለላቸው አበይት ጉዳዮች ውስጥ አብዛኞቹ ጥያቄዎች የሚቀሰቅሱና ድምዳሜያች የሚጋብዙ ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ አንዱ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄን በሚመለከት ያለው ነው:: በኢትዮጵያ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄን አስመልክቶ ፋሽስቱ መንግሥት እስካሁን እያራመደ ባለው ለመቀጠል እንደተዘጋጀ በሕገ—መንግስቱ ረቂቅ ውስጥ ከተጠቀሱትም ሆነ ካልተጠቀሱት ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም:: ለምሳሌ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሁሉም ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩበት አሃዳዊ መንግስት ነው" [አ.1 ቁ1]፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በአስተዳደር አካባቢዎችና በራስ— ገዝ አካባቢዎች የሚዋቀር አሀዳዊ መንግሥት ነው" [አ.60]፣ "በ ሕ.ዲ.ሪ.ኢ. የመንግስት አካላት አደረጃጀትና አሠራር በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሀ ላይ የተመሠረተ ነው" [አ.4 ቁ1] የሚሉት አራ ቀጸች እንደሚጠቁሙት ፋሽስቱ መንግስት ካለሕዝቡ ተሳትፎ እራሱ አቅጣጫውንና አማራጩን ወስኖ ደንግጓል::

"የአስተዳደር አካባቢና የራስ—ገዝ አካባቢ"ሸንጎዎች ወይም አካላት የተሰጡትም ከተዘረዘሩላቸው ሥልጣንና ተግባራት [አ.96—97] የማዕከላዊ መንግስትን እና የብሔራዊ ሸንጎውን ሕጎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች "በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ" ከሚለው ሌላ ይህ ነው ሊባል የሚችል ጉልህ "ሥልጣንና ተግባር" አላቸው ማለት ያዳግታል:: ይህ በሕግ—መንግስቱ ውስጥ የተጠቀሰው ጠባብ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ነው እንግዲህ ምናልባት ቀር የሚለው ወይም በትክክል መጠበቅ ያልታከተው ቢኖር የራስ—ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች የሚኖራቸው የተለየ ሥልጣንና ተግባር ካለ ወደፊት በብሔራዊ ሸንጎው የሚወሰን ይሆናል የሚለው አንቀጽ [አ.100] እንደማስተዛዘኛና እንደየተከፋ—እንጀራ የተለገሰው::

"የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት" የሚባለውም በመጋቢት ወር 1975 ዓ.ም በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን እስካሁን "ታሪካዊ ግኝቱን" እና "የራስ—ገዝ አካባቢያች ክልሎችን" ይዞ ብቅ ያለበት ካለምክንያት አይደለም:: ይህም፣ ሥራው እስካሁን ያልተጠናቀቀ በመሆኑ፣ ወይም በሕግ—መንግስቱ ረቂቅ ላይ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ከሰፈሩት መሠረተ ሃሳቦች ሳይጣጣም በመቅረቱ ሳይሆን፣ የተዘጋጀውን ነገር የሚቋቋመው ብሔራዊ ሸንጎም ተቀባይ ትኖ ውጤት ነው በሚል የሸንጎውን ማህተም ለማከል የታቀደ በመሆኑ ነው የዘገየው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም:: ያም ሆነ ይህ ግን ፋሽስቱ መንግስት ሕ.ዲ.ሪ.ኢ. ማሚባ ለውም አማካኝነት የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄን አስመልክቶ እስካሁን ያራምድ ጋ ነበረው ፖሊሲው ይቀጥላል ማለት ነው:: ችግሩም እንዲሁ::

ገሀዱን ነገር ሁሉ እዚህ መጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ ባይገኝም አንድ ነጥብ ጠቀም አድርጉ ለማለፍ ያህል ግን ፋሽስቶች እንመሰርታለን የሚሉት ሪፐብሊክ /መንግስት የጊ.ወ.አ. ደርግ፣ የኢሰፓአኮ፣ ቀጣይ የኢሠፓም ግልጽ በመሆኑ ህገሪቱን የሶቭየት ዩኒየን ~~የአፎ አዞር ቀኝ-ገዛቶች አይርጉ በማስቀጠል ረገድ አነመንግስቱ ን/ማር ያደ ሏንዓፍሡም~~ የሚዘናጉበት ጉዳይ አልሆነም:: በሕግ—መንግስቱ ረቂቅ ውስጥ የውጭ ፖሊሲን አስመልክቶ ከተጠቀሱት የተለመዱ መርሆዎችና አቋሞች መሐል "የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር <u>ሁለገብ ግንኙነትና ትብብር</u> ያዳብራል ...." [አ.29. ቁ1፣ ሠረዝ የተጨመረ] የሚለው ቀጥተኛ ትርጉሙ ከሶቭየት ጋር ያለው የቅኝ ገዥ—ተገዢ ግንኙነትና ትብብር" ሁለ—ገብ በሆነ መንገድ [ማለትም በርዕዮተዓለማዊ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ወታደራዊ፣ ባህላዊ ወዘተ መስኮች ሁሉ] ይቀጥላል፣ ይስፋፋል፣ ይጠናከራል ማለት ነው::

ሲጠቃለል፣ የፋሽስቱ ጥርቅም አመሰርታለሁ የሚለው ሪፐብሊክ ሆነ ለዚሁ መሠረት ይሆነኛል ብሎ የነደፈው ሕግ—መንግስት የረዥም ግዜ ትያትሩ የወቅቱ ትርዒት እንጂ ከቶም ሌላ ሊሆን አይችልም:: ፋሽስቶች አሁንም "ሕዲሪኢ"፣ "ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት" ወዘተ በማለት እራሳቸውን ለማታለል የመሞከር "መብታቸው" የተጠበቀ ነው:: ሕዝቡን ለማሞኘትና ለማደናገር ግን የሚሆንላቸው፣ የሚቻላቸው አይደለም:: እንዲያውም ሕዝቡ ፋሽስቶች ለሚያደርጉት ማስገደድ እምቢኝ፣ ለጥይታቸውም የጥይት መልስ እየሰጠ የሚሄድበት እንጂ ትጥቅ የሚፈታላቸው አልሆነም፣ ሊሆንም አይችልም::

የሕገ—መንግስት ጉዳይ ክብደት ያለው ጉዳይ ነው:: ምንም እንኳን ሕገ—መንግስት ባለበት ሁሉ ሕግ ይከበራል፣ እንዲሁም በፅሁፍ የሰፈረ ሕገ—መንግስት በሌለበት [ለምሳሌ እንግሊዝ፣ እስራኤል፣ ኒውዚላንድ ወዘተ] ሕግ—አልባነት ሰፍኗል ባይባልም፣ በተለይ አርጊውን ስርዓት ደምስሶ በአዲስ ስርዓት ለመተካትና ይህንንም ለመገንባት ለሚታገል ሕዝብ ለዚሁ ተስማሚ የሆነ ሕገ መንግስትን መሠረት አርጉ መጓዙ አስፈላጊና ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እምብዛም አከራካሪ አይደለም:: የከርከሩ ጉራ በግልፅ የሚለ የውጊን

ያ ሕገ—መንግስት የማንን ጥቅም ያስጠብቃል /ያራምዳል፣ የማንን መብት ያስጠብቃል፣ የማንን ስልጣን ያረጋግጣል፣ በማንና እንዴት ይነደፋል/ይፀድቃል፣ በማንና እንዴት በስራ ላይ ይውላል/መዋሉም ይረጋገጣል ወዘተ በሚሉት አበይት ጥያቄዎች ላይ ሆኖ ይገኛል::

ኢህአፓ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ /መንግስትን በኢትዮጵያ የመመስረት ጉዳይ ይሁን ሕገ—መንግስትን የመንደፍ ጉዳይ በእኔ አውቅል ሃለሁ፣ወይም በእኔ አወክል ሃለሁ የሚካሄድ አይደለም ብሎ በፅኑ ያምናል:: በዚህ ረገድ በፕሮግራሙ በግልፅ [አ.2] እንዳስቀመጠው ከሚታገልላቸው አበይት ጉዳዮች አንዱ የሰፊው ሕዝብ እውነተኛ ወኪሎች የሚሳተፉበት የሀገሪቷ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚሆን የሀገር-አቀፍ ሸንጎ ለመመሥረት ነው:: ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት መምረጥም ሆነ ሕገ—መንግስትን የመንደፉ ስልጣንና ተግባር የዚሁ አገር-አቀፍ ሸንጎ እንደሆነም በግልፅ ያስቀምጣል:: ስለሆነም እንኳንስ በፋሽስቶቹ ጥርቅም የተነደፈ ሕገ—መንግሥቱ ጎ/ማር ያምኔ ይቅርና ሌላ ከዚህ ውጭ በአውቅል ሃለሁ/አወክል ሃለሁ የሚመከር "ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ—መንግስት" የሚባል ነገርን፣ ሺ ግዜ ቢኳኳል፣ ሺ ግዜ በነጋሪትና ማርሽ ቢታጀብ፣ የሚቀበለውም ሆነ የሚጋተው አይሆንም፣ የሚታገለው እንጂ::

በመሠረቱ ሃቀኛው ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በኢትዮጵያ የሚመሠረተው፣ እውነተኛው የኢትዮጵያ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሕገ—መንግስት የሚነደፈና በስራ ላይ መዋሉም ሊረጋገጥ የሚችለው የኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ በተካበረው፣ በረዘሙና መራራ ትግሉ ጠላቶቹን ደምስሶ የሙሉ ስልጣን ባለቤት በመሆን በሚያደርገው ቀጥተኛና ሁለገብ ተሳትፎ ነው:: ስለሆነም መብት በስጦታ፣ ሰላምና ብልፀግና በምፀዋት፣ አርነት በለመና፣ ወዘተ ከቶም ስለማይገኝ ሰፊው ሕዝብ ትግሉን እያስተካበረ፣ ደረጃ በደረጃ እያሰፋና እያጠናከረ ከመቀጠል በስተቀር ሌላ አማራጭ፣ ሌላ መድህን የለውም፣ ሊኖረውም አይችልም:: አሁንም ለፋሽስቶቹ የወቅቱ በማር-የተለወሰ መርዝ ፍቱን ማርከሻው ይህ ብቻ ነው::

—ሰፊው ሕዝብ በፋሽስቶቹ "ሕዲሪኢ"፣ "ሕገ—መንግስት"... ማደናገሪያዎች ትጥቁን አይፈታም!

—የሰፊው ሕዝብ ትግል እስከዘላቂው ድል ይቀጥላል!

—እ ና ቸ ን ፋ ለ ን !!